# ለሞት የቀረበ
## ክፍል ሁለት

፩

ከበልጅግ አሊ

. . . . አሁንም መስኮቱ አጠገብ እንደቆምኩ ነው።ከጠቆረው ሰማይ ጋር የጠቆረው የሥቃይ የወጣትነት ዘመናችን ተመሳስሎብኝ በወርሃ ጥቅምት የደረሱትን አሳዛኝ ታሪኮች እያስታወስኩ እንደገና በትካዜ እቆዝማለሁ ። ኮምፒውተሩ እንደልማዱ ተከፍቶ ፓልቶክ ላይ አንዲት ሴት “ሞት ለኢሕአፓ“ ብላ ትጮኻለች ። በእሷ ጩኸት ምክንያት ልቤ ያንን የቀይ ሽብር ወቅት እያስታወሰ ተጨንቋል።

መውጫ በሌለበት ትንሽ ክፍል ውስጥ በብዛት ተጠቅጥቀን፣ በተወለድንበት ምድር እንደ አውሬ ተቆጥረን ፣ የእግራችን ቁስል መግሎ ፣ ሽቶ ፣ ዛሬ እንገደል ወይም ነገ ሳይታወቅ እየተሳቀቅን የኖርንበት ሁኔታ በሙሉ ትዝ ብሎኛል ። ያንን ግፍ ይሰሩ የነበሩ የደርግ ካድሬዎች አሁን የት እንዳሉ ባላውቅም አዲስ የሕይወት ታሪክ ለራሳቸው ፅፈው ኑሯቸውን እንደሚገፉ አልጠራጠርም ። በተለይ በአሁኑ ውጥንቅጡ በወጣ ፖለቲካ ውስጥ ቦታ ይኖራቸውም ይሆናል ። ማን ያውቃል አንድ ቀን ታሪካቸው ተከትሎ አስኪያጋልጣቸው ድረስ ተመልሰው ስልጣን ላይ ለመውጣት ጥረት እያደረጉም ሊሆን ይችላል ። የተሳካላቸውም ሊኖሩ ይችሉ ይሆናል ።

ሴትየዋ የምትጮኽበት ክፍል ውስጥ ጥቂት ሰዎች ተቀምጠው ይሰሚታል ። በርቺ ! በርቺ ፣ ብለው የሚፅፉም አሉ ። ሌሎች ደግሞ አውራ ጣታቸውን ወደ ላይ በመቀሰር ድጋፋቸውን ይገልጹላታል ። ይህንን ስመለከት አረመኔዎቹ የደርግ ካድሬዎች ታወሱኝ ። ምን አልባት እነርሱም አሁን ከኮምፒውተሩ ጀርባ ሆነው ሞትን እንደገና ይመኙልን ይሆናል ። እንደገና ሁላችንንም ቢችሉ ሰብስበው ለማቃጠል ይሞክሩ ይሆናል ።የሰው ልጅ ከዛ አስቃቂ ኢሰብአዊ ጭፍጨፋ ካልተማረ ከምን ሊማር ይችላል ። . . . . . ምክንያታቸው ምን እንደሆነ ለማሰብ ሞከርኩ ። ጥላቻ ?. . . . የቆየ ቂም ? . . . (የሰሩት ግፍ አላስተኛ ስላላቸው? - - - ለጥያቄዎቼ መልስ አገኝ ይመስል ወደ ዶስቶዮቭስኪ መጽሐፍ ውስጥ ተመለስኩና ታሪኩን ማሰላሰል ጀመርኩ ። ራስኮልኒኮቭ ሰዎቹን ከገደለ በኋላ ለምን ተጨነቀ ?. . . . ለምን ቅዠት ውስጥ ገባ ?. . . . . ከዛ ጭንቀት ውስጥ እንዲወጣ የወሰደው መንገድ ምን ነበር ?. . . . . . አራጣ አበዳሪዋን መጥፎ ሰው ነች ብሎ ለማጥላላት መሞከሩ ጭንቀቱን አቃለለት ወይስ ወደ ባሰ አዘቅት ወሰደው ? . . . . . የሰው ነፍስ በግፍ ያጠፋ ሰው የሠራውን ግፍ አምኖ ይቅርታን ካልጠየቀ ፣ ፍርዱን የተዘጋጀ ካልሆነ ፣ ደስተኛ ይሆናል? . . . . . .ብዙ ጥያቄዎችን ማሰላሰል ያዝኩ ። ግን መልሱ ግልፅ ነው ፈገግ አልኩ። እነዚህ ሴትየዋን አበጀሽ ብለው የሚያጅቡ አረመኔዎች ፣ የጥላቻ ኅተራዎች ምንአልባት ዕድሉን ቢያገኙ በድጋሚ የግፍ ሰይፋቸውን ከመምዘዝ የማይመለሱ የሰሩትን ስህተት ከማመን ይልቅ በጀመሩት መቀጠልን የመረጡ መሆናቸውን ቁልጭ ብሎ ስለታየኝ የጨፈገገው ቀን የባሰ በሃዘን የጠቆረ መስሎ ተሰማኝ ። ጨለማ ወደነበረው ዘመን በኅሳቤ ሙሉ በሙሉ ተመለስኩ ።

በክፍል አንድ በመኪና ተጠቅጥቀን ወደ ቀበሌ 07 እንደተወሰድን ገልጬ ነበር ያቆምኩት ። በከርቸሌ የነበርነው የልደታ ልጆች ወደ ከፍተኛ 22 ቀበሌ 07 እንድንወሰድ መወሰኑን ሲነገረን ሁላችንም የሕይወታችን የመጨረሻው ጉዞ እንደጀመርን ነበር የተሰማን ። የምናውቀው ጉዳይ ቢኖር ከመካከላችን አንዳንዶቻችን እንደምንገደል ነው ። ምንአልባትም ሁላችንም እንሞት ይሆናል ። ሞት ቀላል ነው ። አንዳንድ ሰዎች መሞት ቆራጥነትን ይጠይቃል ሲሉ ይገርሙኛል ። ለእኔ በዛ ወቅት ከባድ የነበረው በዚህ ፍትህ በጎደለበት ፣ አረመኔዎች በነገሱበት ፣ እርጉዝ ከነልጇ በተገደለችበት ፣ እናት የልጇን አስከሬን እንዳታነሳ በተከለከለችበት ፣ የሰው ሥጋ በእሳት በተቃጠለበት ፣ ሽማግሌ ልጅህን አምጣ ተብሎ በተገረፈበት ፣ ሕጻናት ያለ አባት ፣ ሴቶች ያለ ባል ፣ አሮጊቶችና ሽማግሌዎች ያለ ልጅ በቀሩበት ፣ ሃይማኖተኞች በሃይማኖታቸው ምክንያት ፣ ሃብታሞች በሃብታቸው ምክንያት በተገደሉበት ፣ግፉ ተዘርዝሮ በማያልቅበት ዓለም ውስጥ ለመኖር መጣር ነበር ከሞት የበለጠ ቆራጥነትን የሚጠይቅ ሁኖ ያገኘሁት። ደርግ ፅሕፈት ቤት

የደረሰብን ሥቃይ ሳይበቃ አሁን ደግሞ ለሌላ አዲስ ስቃይ መጠራታችን ሕይወታችንን እንድንጠላው ነበር ያደረገን ። ቀበሌው ግቢ ውስጥ ስንገባ ሁላችንም ከመኪናው እንድንወርድ ታዘዝን ። ሦስት ከኢሕአፓ ወደ ደርግ የገቡ አንጃዎችና በዛ ያሉ አውቶማቲክ መሳሪያ የያዙ አብዮት ጥበቃዎች ተቀበሉን ። አንጃዎቹ ኮማንደር ቴዲ( ቴዎድሮስ) ፣ ሳሙዔል ፣ ቢኒያም የሚባሉ ነበሩ ።

- ኮማንደር ቴዲ በኢሕአፓ ውስጥ የእስኳድ ኮማንደር ነበር ተብሎ በትልቁ የተወራለት ሲሆን አጭር ሆኖ መልከ መልካም ነበር። በጠባዩ "መልካም" ( ከሌሎቹ ሲወዳደር) ሲሆን ከፍርሃትና እራሱን ለማዳን ሲል ብቻ ይህንን አረመኔያዊ ተግባር የሚፈፅም ይመስል ነበር። በፖለቲካ እውቀቱም ቢሆን በጥሩ ሁኔታ ላይ የሚገኝ ቢሆንም አዲሱን አቋሙ ጋር እራሱን ለማስማማት የሚያደርገው ጥረት በቀበሌው ማይም አብዮት ጥበቃ አባላት ይደነቅለት እንጂ በሌሎች እስረኞች እምብዛም አዋቂ አላስባለውም።በእስር ቤቱ ውስጥ በዕውቀትም ይሁን መጽሐፍ በማንበብ ብዙ ከሱ የተሻሉ ነበሩበትና።

- ሳሙዔል - የከፍተኛ 3 አደገኛ አንጃ የነበሩት የነ ቴዎድሮስ በላይነህና የነ ቴዎድሮስ አየለ የቅርብ ጓደኛ ሲሆን ጠይም ሆኖ ሰውነቱ ደልዳላ ነበር ። ከመግረፍ ብዛት እጁ ጡንቻ እንዳወጣ ያስታውቃል። ፊቱ ሳቂታ ሲሆን በውስጡ ግን ጭካኔን እንዳዘለ ያሳብቃል። የመግረፉ ሥራ ሙሉ በሙሉ በእሱ ላይ የተጣለ ነው። ለማንም ቢሆን ርህራሄ የለውም።የእስኳድ አባል ነበርኩ የሚል ሲሆን አንጃ ሆኖ ባገኘው ጥቅምና ታማኝነት በጣም ደስተኛ ነበር። ታማኝነቱን ለማሳየት ብዙ አረመኔ ተግባራትን ይፈፅም ነበር።

- ቴዎድሮስ በላይነህ ችኩልና ልታይ ልታይ ባይ ነበር ።ከደርግ ጋር ከተሰለፈ በኋላ ሰንጋተራ የሚገኘው ከፍተኛ 3 ቀበሌ 53 ውስጥ በተደረገው አሰቃቂ ጭፍጨፋ ላይ የተሳተፈና የመራ ነበር ። ሽጉጡን እያሽከረከረ እስረኞችን በጥይት ይመታ ስለነበር በቀበሌው እስረኞች "ሪንጎ" የሚል ቅፅል ስም ተሰጥቶታል።

- ቢንያም - ቀይ፣ወፍራም ሲሆን የፊቱ ጠባብነት የእንቁራሪትነት ገፅታ ሰጥቶታል። ኮርማ የሚል ቅፅል ስም ነበረው።ምክንያቱም ከሴቶች እስረኞች ጋር ካለፈቃዳቸው መዳራት ስለሚያበዛ ነው። በእስረኛው ሁሉ የተናቀ ሲሆን እስረኞች ማሰቃየት የሚያስደስተው ነው ። የጭንቅላቱ ችሎታም አነስተኛ መሆኑን ማወቅ በጣም ቀላል ነው።

የቀበሌ 07 እስር ቤት አንድ የተወረሰ ትልቅ ቤት ሲሆን በጎን በቆርቆሮ የተሰራ የወንዶች ክፍል አለው። ከኋላ ደግሞ የትልቁ ቤት ማዕድ ቤት የነበረው የሴቶች እስረኞች መታሰሪያ ሆኗል። ከሱ ጎን ደግሞ አንድ ሌላ አነስተኛ የወንዶች እስር ቤት አለው። በቆርቆሮ የተሰራው የወንዶች እስር ቤት ውስጥ ያሉት እስረኞች አደገኛ ያልተባሉና የመፈታት እድል ያላቸው ከአውራ ጎዳና መስሪያ ቤት " ቢሮክራት" ተብለው በመሥሪያ ቤቱ ካድሬ እንዲታሰሩ የተወሰነባቸው ሠራተኞች ነበሩ። ( ብዙዎቹ የተማሩና ለመሥሪያ ቤቱ በጣም አስፈላጊ የነበሩ ናቸው ። ) ሽንት ቤቱ በወንዶችና በሴቶች እስር ቤት መካከል ያለ ሲሆን በጣም ቆሻሻና ሊፈርስ የደረሰ ነበር።ትልቁ ቤት ብዙ ክፍሎች ያሉት ሲሆን አዲስ የመጡና አደገኛ ተብለው የተፈረጁ እስረኞች የሚታሰሩበት አንድ ጠባብ ክፍል አለው።ይህ ክፍል ነበር "ሶደሬ" በመባል የሚታወቀው። ሳሎኑ ደግሞ ለቀበሌ መሰብሰቢያነት ይገለገሉበታል። መኝታ ክፍሎቹ ለመግረፊያና ለቃል መስጫነት ያገለግላሉ።
በመጀመሪያ ሳሎኑ ውስጥ ከተቀመጥን በኋላ ሁላችንም ወደ ሶደሬ እንድንገባ ታዘዝን ። ሶደሬ ውስጥ የቁስሉ ሽታ አፍንጫችንን ሞላው ።ሶደሬ ውስጥ የገባ በሞላ ለሞት እንደቀረበ ይሰማዋል ። ብዙዎቹ እስረኞች ነፍሳቸው አትውጣ እንጂ ከሞቱት በላይ

ከቆሙት በታች የሆኑ ነበሩ። እግዜር እህል ውሃችሁ አይለቅ ብሎ ቢተርፉ እንኳ የቀረ ሕይወታቸውን አካለ ጎደሎ ሆነው እንደተሰቃዩ እንደሚኖሩ የታወቀ ነበር ።

ቀደም ብለው የታሰሩ እስረኞች በየምክንያቱ እየመጡ ይመለከቱናል ። የሚያውቁን ሰላም ይሉናል ፣ የማያውቁን ፈገግ ብለው ይሄዳሉ ። ሶደሬ ውስጥ የነበሩ እስረኞች በእንክብካቤ ተቀበሉን። የቆሰሉት እንኳን እግራቸውን በእጃቸው እየጎተቱ ጠጋ ብለው ሊያስቀምጡን ሞከሩ ። አንዳንዶቹ ምንም እንኳ ሊያፅናኑን ቢሞክሩም ዓይናቸው በእንባ ሞልቶ ሲታይ ምን እንደሚጠብቀን በግልጽ ይናገር ነበር ። የሌሎቹ ደግሞ ተስፋ የቆረጠ ሁኔታቸው ለምንም ነገር እንዳንጨነቅ ይገፋፈን ነበር ። ያላቸውን ምግብና ፍራፍሬ ቢሰጡንም ሁላችንም ምንም ልንበላ አልቻልንም። በዛች ሞት ባንዣበባት ክፍል ውስጥ ለዘላለም የማይረሳ ወንድምነታቸውን አሳዩን።የሰው ልጅ ክፉም ደግም ባሕርይ እንዳለው መረጃ ሆኑን።ሰብዓዊነት በጠፋበት ዘመን ሰባዓዊነታቸውን አጉልተው አሳዩን ።

በመጀመሪያ ሁሉም የኢሕአፓ አባላት መስለውን ነበር ግን እየቆየ ስንሄድ ምንም እንኳ ብዙሃኑ የኢሕአፓ አባላት ቢሆኑም የጀሆቫ ሃይማኖት ተከታዮች ፣ ከበርቴ ተብለው የታሰሩ ፣ ካለምንም ምክንያት በጥላቻ የታሰሩም እንዳሉበት ተረዳን ። በዚያ ሞት በቀረበበት እስር ቤት ውስጥ ሁላችንም በፍቅርና በሃዘኔታ ነበር የምንተያየው ። በተለይ የጆሆቫ እምነት ተከታዮች የነበሩት ለእኛ ያሳዩን የነበረው ፍቅር የተለየ ነበር። ብዙዎቻችን ይህንን ሃይማኖት የማናውቀው ቢሆንም ለሃይማኖቱ ጥላቻ እንደነበረን የታወቀ ነው ።

እስር ቤት ውስጥ ብዙ የሰማነው ትንሳዔና ከሰተ ሰለሚባሉ የደርግ አረመኔ ካድሬዎች ነው ። የሰሩትን ግፍ ላዳመጠ የሰው ፍጡር ናቸው ብሎ ለማመን ይቸገራል ። ወደ ምሽት አካባቢ እንደተጠበቀው ከሰተና ትንሳዔ መጡ ።

- ከሰተ - ለብዙ ዘመን በልደታ አካባቢ አረመኔነቱ የተወራለት ነው ።ቀይና ቀጭን ሲሆን ሙሉ ጅንስና የዘመኑ የተራማጆች መግለጫ የነበረውን የሌኒን ኮፍያን ያዘወትራል። የፊቱ ሹልነት ተንኮለኛነቱን አጎልቶ ያሳያል። ከሰተ መሣቅ ከጀመረ ለእስረኞች በቅርብ ቀይሽብር መኖሩ የሚያሳይ ምልክት ነው ተብሎ ስለሚነገር ሣቁ በእስረኞች መካከል ፍርሃትን ያመጣል ። ጥሩ ሥራና ደሞዝ ነበረው ተብሎ በሰፊው ይወራለታል። በልዩ ልዩ ምክንያት ከታሰሩ እስረኞች የተወረሰ መኪና ሲነዳ አጠገቡ ኡዚ የሚባል አውቶማቲክ መሣሪያ አይለየውም ። አሁን አዲስ አበባ ውስጥ ከእስር ተፈቶና ዓለም አቀፍ በሆነ መስሪያ ቤት ተቀጥሮ ይሠራል የሚል ሰምቻለሁ ።

- ትንሳዔ የአንበሳ አውቶቢስ መሥሪያ ቤት ካድሬ የነበረች ሲሆን ጠይም ሆና መልከ መልካም ነበረች ። አረመኔነቷን የማትደብቅና በሰዎች ጭካኔ የምትደሰት ነች ። በተለይ በተወሰኑ እስረኞች ላይ ያለት ጥላቻ የጎላ ነው ።

ትንሳዔ የተገረፈ እስረኛ እግር ላይ በመቆም ማሰቃየት እንደምትወድ ሰምተን ነበረ። እንደተባለውም እንደገባች የተገረፉትን እስረኞች እግር ላይ እየቆመች ፣ የመገለ ቁስላቸውን እየረገጠች ፣ እስረኞቹን እያሰቃየች በሰለለ ድምፅ ትስቅ ጀመር። ከሰተ ግን እንደመጣ ከከርቸሌ ከመጣነው ውስጥ በሁለቱ ላይ ትኩረት አደረገ -- በደሳለኝና ውብሸት ላይ ። ከሰተ ለትንሳዔ አንድ ዓይና የሆነውን ውብሸትን እየጠቆመ ይኼ እኮ ነው የዛ እርጉም ወንድም ብሎ አሳያት። ወዲያው ሁላችንም አበበ አለማየሁን ማለቱን መሆኑን ተረዳን <u>።(“ተራራውን ያንቀጠቀጠ ትውልድ“ በሚለው መጽሐፍ ውስጥ የወያኔ ባለሥልጣን የሆነው ሰለሞን ተቀባ ወያኔን ከመደባለቁ በፊት ለደርግ ሲሠራ ውብሸት አለማየሁን ማሲያዙን አስተባብሎ ፅፎት ይገኛል ። በዛ ወቅት ግን እሱ እንዳሲያዘው ለአካባቢው የኢሕአወሊ መዋቅር ግልፅ ነበር)</u> ።

አበበ አለማየሁ እኛ ከመምጣታችን በፊት በእነ ከሰተ የተገደለ የውብሸት አለማየሁ ወንድም ነው። ትንሳዔ ውብሸትን ቂም ባዘለ አመለካከት አየችው፡፡ በሁላቸንም ውስጥ ነገሠ። ውብሸት ከሁላችንም በላይ አደጋ ውስጥ መሆኑ በዚያች ሰዓት እርግጠኛ ሆንን።

ትንሳዔ ዕውቀቷ አነስተኛ ነበረ ። በትምህርትም የገፋች አልነበረችም ። ግን በወቅቱ የካድሬዎች መመዘኛ የነበረውን የአብዮት ቋንቋ በቃሏ አጥንታ ይዛ በማይገባበት ቦታ እየደነቀረች የምታስካካ የወቅቱ የአብዮተኞች ንግሥት ነበረች። ሶደሬ የተባለው የቀበሌ 07 እስር ክፍል በመጣች ቁጥር ሁልጊዜ ወደተለመደው ክርክሯ ታመራለች።ጆሆቫዎችን "ሞት ለኢሕፓ" እንዲሉ ትጠይቃቸዋለች ። እንደተለመደው ጆሆቫዎቹ አንልም አሉ ። ታስፈራራቸዋለች ፣ እንደሚገረፉ ትነግራቸዋለች ፣ ቀይሽብር እንደማይቀርላቸው ትፎክራለች። ይባስ ብለው ትንሳዔን መጽሐፍ ቅዱስን እየጠቀሱ ይሟገቷት ጀመር።ትንሳዔም ሰለማታውቀው መጽሐፍ ቅዱስ ስታወራ ለሰማት የሠይጣን ቁራጭ እንጂ ከዚህ በፊት ሃይማኖት ኖሯት የምታውቅ አትመስልም ። መጽሐፍ ቅዱስ የገዢው መደብ መጨቆኛ መሣሪያ ነው ፣ የኢምፔሪያልስቶች ቲዎሪ ነው በማለት ትንሽ ከሰበከች በኋላ መከራከር ከፈለጋችሁ ብርሃኑን ከቀበሌ 02 እንጠራላችኋለን ብላ ታፌዛለች ።

ብርሃኑ - የከፍተኛ 22 ቀበሌ 02 ተመራጭ ሲሆን ፊቱ ከሰውነቱ ጋር ሲወዳደር በጣም ትልቅ ነው ። ከአብዮቱ በፊት የጴንጤ ሃይማኖት ተከታይና በኃይማኖቱ ውስጥ የሰባኪነት ስልጣን የነበረው ሰው ነበር ። የሚያውቁት የተዋጣለት ሰባኪና በልሳን የሚናገር እንደነበር ይናገራሉ ። አብዮቱ ሲፈነዳ ደግሞ ወደ አብዮተኝነት ተለውጦ የቀበሌ ተመራጭ በመሆን ውስጥ ተመርጦ በቀይ ሽብር ሰሞን አብዮተኝነቱን ለማሳየት ቀና ደፋ የሚል ነበር ። በፀሎት ቀን ሲያደርገው የነበረው የወንጌል ስብከት ልምድ ለአብዮታዊው ቅስቀሳው ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርጎለታል። በተለይ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ አድሃሪነት፣ የካፒታሊስት መጨቆኛ መሣሪያ መሆን ፣ አብዮትን በሃይማኖት በሚቃወሙት አካባቢ ቅስቀሳ የሚያደርግ ነበር። በአብዮቱ ውስጥ ተጠምቆ አዲሱን ምስክርነት በሰፊው ተያይዞት ነበር ።

ጆሆቫዎቹ ግን ፊታቸው ላይ የነበረው ቆራጥነት በግልጽ እየታየ "ማንም ይውደም" ፣ "ሞት ለኢሕአፓ" አንልም ብለው ፍርጥም አሉ ። የወቅቱን የፋሽሽቶች ትምክህት ከጀግኖቹ የኢሕአፓ ወጣቶች ጋር መጋፈጣቸው አሁንም ቢሆን በጣም የሚያስገርመኝና በኩራት የምተርከው ነው ። ትንሳዔም ግን የነሱን ቆራጥነት የኢምፔሪያሊዝም ሴራና ከሲ. አይ . ኤ ቅጥረኝነት ሌላ ልትመለከተው አልቻለችም ። ለትንሳዔ በዛ ወቅት የሚያምኑበትን የእግዜር ቃል መፈፀማቸው ሳይሆን የአሜሪካን ተላላኪ መሆናቸው ነበር ጎልቶ የታያት ። በማይም አንደበቷ አያችሁት በኢሕአፓና በዚህ በኢምፔሪያሊስት ሃይማኖት መካከል ያለውን መተባበር በማለት ትልቅ ምስጢር የተገለፀላት ይመስል ታስካካም ነበር ።ብዙዎቻችንን በነዚህ ሰዎች ላይ ከፍተኛ አደጋ ይደርስ ይሆናል በሚል ስጋት ተቆራምደን ተቀምጠን ፣ በሃሳብ የእሷን የማይረባ ትንታኔ እየሰማን እንጨነቅ ነበር ።

ብዙዎቹ የሲ.አይ .ኤ ቅጥረኛ ብለው የንፁሕ ዜጎችን ደም ሲያፈሱ የነበሩ ካድሬዎች ፣ ደርግ ከሥልጣን በወደቀ ጊዜ ከኢትዮጲያ በመውጣት የተለያዩ የፈጠራ ታሪክ በማዘጋጀት ፣ ዛሬ ዛሬ "ኢምፐሪያሊዝም" እያሉ ባወገዙት ሃገር ውስጥ ተቀምጠው ያንን ያሰቃዩትንና የገደሉትን ትውልድ አሁንም እንደ ፓልቶክ ባሉ መገናኛ ዘዴዎች ሲያወግዙ ይሰማሉ። ይህ የፍትሕ ያለህ እያለ የሚጮህ ሃሳብ ነው እንደዛሬ ያለውን ቀን የባሰ የሚያጠቁረው።

ሌላው በዛ እስር ቤት ውስጥ የነበሩ ደግሞ ከበርቴ ተብለው የታሰሩ ግለሰብ ነበሩ ። የዕቃ ማመላለሻ ከባድ መኪናና፣ የንግድ ቤት ነበራቸው። የቤተሰብ ሃላፊና የትንንሽ ልጆች አባት በመሆናቸው ብዙውን ጊዜ ስለ ልጆቻቸው ያወሩን ነበር። ከገጠር እንዴት እንደመጡና አዲስ አበባ ሥራ እንደጀመሩ፣ ከዛም ትንሽ ሃብት እንዳገኙ አጫውተውናል። እሳቸው እዛ እስር ቤት ውስጥ የሚያሳልፉትን ሰዓት እንደከሰረ ጊዜ ነበር የሚቆጥሩት። ብዙዎቻችን የወቅቱን ሁኔታና በእሳቸው ላይ ያንዣበበውን ችግር ፣ የአሳሪዎቻችውን እውነተኛ ባህሪ እንዳልተረዱት ስለገባን ከልባችን እናዝንላቸዋለን ። ገር ፣ ቀና ፣ ሃይማኖተኛና ሰውን አክባሪ በመሆናቸው በሁሉም እስረኞች የተወደዱ ነበሩ። ያላቸው ንብረት ተወስዶ መኪናቸው አንድ ኃይለማርያም በሚባል አረመኔ የ07 ቀበሌ የአብዮት ጥበቃ ሊቀመንበር ተወርሰው በዚያ እስር ቤት ውስጥ ካለጥፋታቸው በፀረ ሕዝብነት ተፈርጀው ነበር።

- ኃይለማርያም ቀይ ሆኖ ረዘም ያለ ሲሆን በቀይሽብር ከሁሉም በላይ የተጠቀመ ነው ። ከበርቴ እየተባሉ የታሰሩትን ሰዎች መኪና ፣ ንብረት እየዘረፈ ፣ ሴቶችን እያማገጠ ፣ ክላሹን ታጥቆ በየቦታው እየዞረ ከቀይ ሽብር ሌላ የራሱን ሽብር የሚዘራ ነበር ። አብዮት በግል ከመጣላቸው ውስጥ ሲሆን በከሰተ የታዘዘውን ሁሉ ለመስራት ወደ ኋላ የማይል ነው ። በግል ይህ ሰው የስንት ሰዎች ደም እንዳለበት መናገር ይከብዳል ። ግን ሁል ጊዜ ከትከሻው የማይለየውን ክላሽን ላየ መሣሪያውን ለጌ/ት ብቻ እንዳሊያዘው ይረዳል ። ኃይለማርያምን በቃላት ለመገለጽ ጨካኝ ፣ አረመኔ የሚሉት ቃላት ብቻ በቂ ናቸው ለማለት ይከብደኛል . . . . .

"ከበርቴ" ተብለው የታሰሩት አዛውንት በክብር ተነስተው ትንሳዔን እጅ ከነሱ በኋላ እባክሽን ለልጆቼ ማንም የላቸውምና ጉዳዬን ቶሎ ተመልከታችሁ ውሳኔ ስጡኝ ። ያጠፋሁትም ካለ ቅጡኝ ። ግን ለልጆቼ ማንም ስለሌለ ቶሎ ልቀቁኝ ብለው ልመናቸውን አቀረቡ። በእሳቸው አስተሳሰብ ይህንን አቤቱታቸውን ሰምታ ፣ አዝና ቶሎ የምትለቃቸው ነበር የመሰላቸው። ግን ለትንሳዔ ትምክህታዊ ፀባይ ይህን ንግግር ምንም አልነበረም። የደነደነን ፋሽሽታዊ ልቦናዋ የሕዝብ ለቅሶ እንደማያላላው የታወቀ ነበር። ከዚህ ደግ ሥራ ይልቅ ለልቦናዋ ደስታን የሚሰጣት በቀይ ሽብር ተመትቶ ፣ በደም ተጨማልቆ በመንገድ ላይ የተጣለን ወጣት ስትመለከት ነው ። ይባስ ብላ የለበጣ ሳቋን አሰምታ "በቅርብ ውሳኔህን ታገኛለህ ። ስለልጆችህ ግን አብዮቱ አለላቸውና አታስብ" አለችና ከክፍሉ ወጣች ። ትንሳዔ በዛ ወቅት እኝህን ሰውዬ ከእስር ፈትታ ከኃይለማርያም መኪናቸውን ወስዳ ለእሳቸው ለመመለስ ፍላጎትም ሃሳብም የላትም ፣ ጓዳዊ ቃል ኪዳኗም አይፈቅድላትም። ምን አልባት ሰውዬው ይህንን አልተረዱትም። በቅርብ ውሳኔህን ታገኛለህ ስላለቻቸው ደስታም ሃዘንም የተቀላቀለበት እንባ ያነቡ ጀመር ። ሲያለቅሱ ስላየን ሁላችንም ታላቅ ሃዘን ተሰማን ። ምንድንው የኚህ ሰው ጥፋት ? ልጆቻቸውን እሳቸው ከታሰሩ ማን ያሳድግላቸዋል ? ንብረታቸውን ወስዶ እሳቸውን መልቀቅ ምንድነው ችግሩ ? ይህ ሁሉ ሃሳብ አዕምሯችንን አናወጠው ።

ከሰተ ከሶደሬ ክፍል ከመውጣቱ በፊት ሳሙዔል የሚባለውን አንጃ ጠርቶ ውብሸትን ገልብጡት ብሎ አዘዘ። እነ ሳሙዔል ውብሸት ላይ እንደ ተራበ አራዊት ተረባረቡበት ። ታማኝነታቸውን ለከሰተ ለማሳየት በአንድ ጊዜ ተቀራመቱት ። በዛ ትንሽ ሰውነት ላይ ፣ በዛ ችግር ባጎሳቆለው ሰው ላይ ፣ የተመረጠ እስረኞች ምግብን እየወሰዱ ሲቀለቡ የቆዩ አራዊቶች ሰፈሩበት ። ምን እንደሚፈልጉ እንኳ አልነገሩትም ብቻ ቀጠቀጡት። ሰው እንዳልሆነ ፣ ከድንጋይ እንደተሰራ አንስተው አፈረጡት ፣ እንዳይናገር አፉን በጨርቅ ፣ እንዳይፈራገጥ እጆቹንና እግሮቹን በገመድ አስረው ሰውነቱ ደም በደም እስከሚሆን ወቀጡት። ሌሊቱን በሞላ በየተራ ሁላችንም እየተጠራን ተገረፍን ። በአንዳንዶቻችን ላይ የነበረው ግርፍ ከደርግ ፅሕፈት ቤት ጋር ሲተያይ ብዙ አልነበረም ። የፋሽሽቶችን የጭካኔ ሱስ ለመወጣት እንጂ ግርፉ ትርጉም ያጣ ነበር።እኛ ከከርቸሌ ወደ ቀበሌ ስንወሰድ የኢሕአወሊ መዋቅር ሁሉም ተጋልጦ ነበር። እነከሰተ የማያውቁት ምስጢር አልነበረም።የጭካኔ ጥማቸውን ለማርካት ግን መገረፍ ነበረብን ። ለትንሳዔ ፣ ለከሰተ ፣ ለኃይለማርያም ፣ ለይግረም ፣ ለለማ ፣ ለደስታ ፣ ለመሳሰሉት የደም ጥማት ያህል።

## ይቀጥላል

ሰለ ተሰውት ዜጎች የሚያስብ በሰላም ይክረም !!!!

beljig.ali@gmail.com